
# የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ መሻሻል መርሀ ግብር ገዥ መመሪያና ማዕቀፍ




ህዳር 2009 ዓ.ም

ትምህርት ሚኒስቴር

ማውጫ


ይዘት ገፅ

መግቢያ ………………………………………………………………………………… 4
ክፍል አንድ፡- የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ መሻሻል መርሀ ግብር ገዥ መመሪያ ……………………………………………………………………….. 6
1.1 የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት መሻሻል መርሃ-ግብር ምንነት፣ አስፈላጊነት እና ዓላማ ………………………………………………………………………………… 6
1.1.1 የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት መርሀ ግብር ምንነት …………………… 6
1.1.2 የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት መሻሻል መርሃ-ግብር አስፈላጊነት ……. 7
1.1.3 የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ መሻሻል መርሀ ግብር ዓላማ ……. 8
1.2 የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ መሻሻል መርሃ-ግብር የትኩረት አቅጣጫ 9
1.2.1 መማርና ማስተማር ………………………………………………………… 9
1.2.1.1 የውጤታማ አመቻቾች ጥረትና ተነሳሽነት ………………………………… 9
1.2.1.2 የተማሪዎች ጥረትና የሚጠበቅባቸው ባህሪያት …………………………… 12
1.2.1.3 ሥርዓተ ትምህርት፡-……………………………………………………… 13
1.2.2 የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ አመራርና አስተዳደር …………… 13
1.2.3 ምቹ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ ሁኔታና አካባቢ …………….. 14
1.2.4 የወላጅ፣ የህብረተሰብ፣ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ ግንኙነት እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አጋርነት ……………………………… 15
1.3 የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ መሻሻል የአተገባበር ስልት ……… 16
1.3.1 ዋና ዋና ስልቶች ………………………………………………………… 16
1.4 የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ መሻሻል መርሃ-ግብርን የሚመራ ኮሚቴ ማቋቋም ……………………………………………………………………….. 17
1.5 የአማራጭ መሠረታዊ ጣቢያ ግለ ግምገማ ማካሄድ ……………………… 18
1.6 ምዘና የአፈጻጸም ትንተና ግብ ማስቀመጥ ……………………………… 18
1.7 የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ መሻሻል ዕቅድ ማዘጋጀት …….. 19
1.8 ሥርዓተ ትምህርቱን በውጤታማነት መተግበር ………………………….. 21
ክፍል ሁለት፡- የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ መሻሻል መርሀ-ግብር ማእቀፍ 22
2.1 የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች ማሻሻል ስታንዳርድ …………….. 23
ዐብይ ርዕሰ ጉዳይ 1፡-መማርና ማስተማር …………………………………… 24
ንኡስ ጉዳይ 1.1፡-የማስተማር ተግባር ……………………………………… 24
ንኡስ ጉዳይ 1.2፡-መማርና ግምገማ ………………………………………… 25
ንኡስ ጉዳይ 1.3 ሥርዓተ ትምህርት ……………………………………… 25

ዐብይ ርዕሰ ጉዳይ 2፦ምቹ የትምህርት ሁኔታና አካባቢ ......................... 26
ንኡስ ጉዳይ 2.1፡- የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ ፋሲሊቲ .............. 26
ንኡስ ጉዳይ 2.2 ተማሪን ማብቃት................................................ 27
ንዑስ ጉዳይ 2.3 ለተማሪ የሚደረግ ድጋፍ ...................................... 27
ዓቢይ ርዕሰ ጉዳይ 3 ፦የጣቢያ አመራር ............................................ 28
ንኡስ ጉዳይ 3.1፡- ስትራተጂካዊ ራዕይ ............................................ 28
ንኡስ ጉዳይ 3.2፡-የመሪነት ባህሪይ .................................................. 28
ዓቢይ ርዕሰ ጉዳይ 4፦የህብረተሰብ ተሳትፎ ........................................ 29
ንኡስጉዳይ 4.1፡- ከወላጆችና ከአሳዳጊዎች ጋር አብሮ መስራት .................. 29
ንኡስ ጉዳይ 4.2፡-ኅብረተሰብን ማሳተፍ፡- ............................................ 29
ንኡስጉዳይ 4.3፡- የትምህርቱን ስራ ማስተዋወቅ ..................................... 30

ተቀጽላዎች ................................................................................ 30
1.1፡- የጣቢያ መገምገሚያ ናሙና ቅጽ ................................................ 30
1.2፡- የሦስት ዓመት ስትራቴጅ ክዕቅድ ማቅረቢያ ናሙና ቅጽ .................. 34
1.3፡-የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ መሻሻል ዓመታዊ የድርጊት መርሃ-ግብር ናሙና ቅጽ ............................................................ 37
1.4፡- የተለያዩ የመማር ፍጥነት ያላቸው ተማሪዎች መከታተያ ቅጽ ................ 38
1.5፡- ተከታታይ የመምህራን ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ስልጠናን / CPD / መከታተያ ቅጽ .......................................................................... 39
1.6፡- የክበባትና የልዩልዩ ፕሮግራሞች እንቅስቃሴ መከታተየያ ቅጽ ............ 39
1.7፡- የተማሪዎች ውጤት መከታተያ ቅጽ ............................................ 40
1.8 የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት መስጫ ጣቢያዎች የማጠናከሪያ ትምህርት መቆጣጠሪያ ቅጽ ............................................................ 41
1.9፡- የሥርዓተ ትምህርት መሣሪያዎች ስለመገምገማቸው መከታተያ ቅጽ ......... 42
1.10፡- ቅጽ ትምህርት ቤቱን የሚረዱ ወላጆች /አሳዳጊዎች/ ብዛት መመዝገቢያ ቅጽ 43

## መግቢያ

ትምህርት ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ ልማት የሚበጁ ዜጎችን ለማፈራት የሚያስችል እና የሕብረተሰቡን አመለካከት ወደ ሚፈለገው አቅጣጫ የሚለውጥ፣ ከአዳዲስ ቴክኖሎጂ ውጤቶችና ሳይንሳዊ ግኝቶች ጋር በማስተዋወቅ ኢኮኖሚያዊ፣ ማሕበራዊና ባሕላዊ እድገቶችን የሚያፋጥን መሳሪያ ነው። በሀገራችንም ትምህርትን የልማትና የእድገት መሳሪያ ለማድረግ  የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ተቀርፆ ሥራ ላይ ከዋለ ወዲህ የሀገራችንን የትምህርት ተሳትፎና ፍትሐዊነት ከማሳደግ አንፃር በሁሉም ደረጃዎች አመርቂ የሆኑ ውጤቶች መመዝገባቸው ይታወቃል። ከዚህ ጐን ለጐን የትምህርት ጥራትንም ለማሻሻል እስካሁን ጉልህ ተግባራት የተከናወኑ ሲሆን፤ አመቻቾችን ማብቃት፣ ሥርዓተ ትምህርቱን በየጊዜው በመፈተሽ ማሻሻል፣ የትምህርትና ሥልጠና አመራርን ብቃት ለማሳደግ ያልተማከለ የትምህርትና ሥልጠና አመራርን ወደ ወረዳ እና ትምህርት ቤት ማውረድ፣ በትምህርት ሥራው የኅብረተሰቡን የባለቤትነት ስሜትና ተሳትፎ ማሳደግ፣ የትምህርት መሣሪያዎችን አቅርቦት ማሳደግና በተለይም የትምህርቱን አሰጣጥ በቴክኖሎጂ ግብዓቶች በመታገዝ የተከናወኑ ተግባራት የሚጠቀሱ ናቸው። በአጠቃላይ በትምህርትቤቶችና በተቋማት ደረጃ ያለውን ትምህርት በተሻለ ጥራትና በተገቢው መንገድ ለመስጠት ከፍተኛ እንቅስቃሴ ተደርጓል።

ሆኖም ከላይ በተጠቀሱት ጥረቶች ብቻ የሚፈለገውን ያህል ውጤታማ ሆኖ መገኘት አልተቻለም። በተለያዩ ጊዜያት የተካሄዱ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በየደረጃው ያሉ ተማሪዎች ውጤታቸው ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል። በተለይ በአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት መስጫ ጣቢያዎች የተማሪዎች ውጤትና የትምህርት አቀባበል ዝቅተኛ ሆኖ ታይቷል።ለዚህም ከሚጠቀሱ ምክንያቶች ውስጥ በዋንኛነት የአመቻቾቹ ለደረጃው የሚመጥን የትምህርት ዝግጁነት አነስተኛ መሆን፣ በቂ ትምህርት ግብአቶች ተሟልቶ አለመገኘት፣ በተለያዩ ምክንያቶች የትምህርት ሰዓት ብክነት፣ በቂ ክትትልና ድጋፍ በየደረጃው ካሉ አካላት አለመኖር፣ ወላጆች ለመርሀ ግብሩና ለጣቢያው የሚሰጡት ግምት አነስተኛ መሆን፣ የሶስት ኣመቱን ትምህርት መርሀ ግብር እድሜያቸው ከ7-11 ለሆኑ ህጻናት መስጠትና የመሳሰሉት ይገኙበታል።  በተጨማሪም በአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ህጻናትን  የትምህርት ውጤት ለማሻሻል የጣቢያዎቹን ስታንዳርድ እንዲጠብቁ የተሟላ ድጋፍና ክትትል ማድረግ የሚያስችል

አደረጃጀት፣ አመራርና አሰራር አለመዘርጋትና የመርሀ ግብሩን አፈፃፀም በየወቅቱ የሚገመግም ስርዓት አለመዘርጋት በጣቢያው የሚሰጠውን ትምህርት ጥራት እንዳይኖረው አድርጎታል። በመሆኑም በአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት የሚሰጠው ትምህርት ጥራቱን የጠበቀ እንዲሆን ለማድረግ ጣቢያዎች መሰረት እንደመሆናቸው አሰራራቸውን ማሻሻል አማራጭ የሌለው ተግባር ነው።

ይህንንም መሠረት በማድረግ፣ በእስካሁኑ ሂደት የተከሰቱ ችግሮችን እና ጉደለቶችን በመመርመር በማስወገድ፣ ጠንካራና መልካም ልምዶችን ለይቶ በማውጣት ጥራት ያለው ትምህርትን በተሻለ ሁኔታ በሀገራችን በሚገኙ የአማራጭ መሰረታዊ ጣቢያዎች ለመስጠት
ልምድ የመቀመርና የተገኘውን ልምድ አስፋፍቶ መጠቀም ትኩረት የተሰጠው ቁልፍ የማሻሻያ አቅጣጫ ተግባር ሆኗል። በመሆኑም ትምህርት ሚኒስቴርና ክልሎች በጋራ በመሆን በጣቢያ ደረጃ የትምህርት ተገቢነትና ጥራትን ለማረጋገጥ እንዲቻል የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ መሻሻል (School Improvement) ማዕቀፍን በማዘጋጀት የማሻሻያ ፕሮግራሙ በሁሉም ትምህርት ቤቶች በሰፊው መተግበር አስፈልጓል፡፡

ይህ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ መሻሻል መርሃ-ግብር አተገባበር ገዥ መመሪያና ማዕቀፍ የመደበኛውን ትምህርት ቤት የማሻሻያ መርሀ ግብር መመሪያና ማእቀፍ መሰረት በማድረግ የአማራጭ ትምህርት ጣቢያ ስታንዳርድና ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ተሻሽሎ የቀረበ ነው።

ይህ ሰነድ ሁለት ክፍሎች አሉት፡፡ ክፍል አንድ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ መሻሻል መርሀ ግብር ገዥ መመሪያ ሲሆን ክፍል ሁለት ደግሞ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ መሻሻል መርሀ ግብር ማዕቀፍ ናቸው፡፡ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ መሻሻል መርሀ ግብር ገዥ መመሪያ በዋናነት ያተኮረው የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ መሻሻል መርሀ-ግብር ምንነትና ዓላማዎች፣የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ መሻሻል የትኩረት አቅጣጫ፣የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ መሻሻል መርሀ-ግብር አተገባበር ስልት፣የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ መሻሻል መርሃ-ግብር የዕቅድ ዝግጅትአተገባበር፣ክትትልና ግምገማ ሲሆን፣ ማእቀፉ ደግሞ በውስጡ የትምህርት ቤት መሻሻል መርሃ ግብር አብይ እና ንኡስ ርእሰ ጉዳዮችን፣

የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችንና ልዩ ልዩ የክትትልና ሪፖረት ማጠናቀሪያ ቅጾችን ይዟል።

# ክፍል አንድ፡- የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ መሻሻል መርሀ ግብር ገዥ መመሪያ


## 1.1 የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት መሻሻል መርሃ-ግብር ምንነት፣ አስፈላጊነት እና ዓላማ

### 1.1.1 የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት መርሀ ግብር ምንነት

የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት መሻሻል መርሃ-ግብር ያለበትን ተጨባጭ ሁኔታ በተለያዩ የትምህርት ቤት ርዕሰ ጉዳዮች አንፃር በመዳሰስ እና ግምገማ በማካሄድ የትምህርት ግብዓቱንና ሂደቱን በማሻሻል ተማሪዎች የላቀ የትምህርት ውጤት እንዲያስመዘግቡ በማድረግ ላይ ያተኮረ ወቅታዊና ጠቃሚ ፅንሰ ሀሳብ ነው።

የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ መሻሻል ዋነኛ ትኩረት የተማሪዎች መማር እና የመማር ውጤት ላይ ሲሆን፣ ለዚህም ስኬት የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎቹ በቅድሚያ ደካማ እና ጠንካራ ጐናቸውን በመለየት በእያንዳንዱ አበይት ርዕሰ ጉዳይ አንፃር ቅድሚያ ትኩረት በማውጣት እና ግብ በማስቀመጥ ሁሉም የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ ማህበረሰብ አባላትና ሌሎች ባለድርሻዎች ለተማሪዎቹ መማርና የመማር ውጤቶች ከፍተኛ መሆን የሚንቀሳቀሱበት የማያቋርጥ ሂደት ነው። የጣቢያው አበይት ርዕሰ ጉዳዮቹም በአራት የተከፈሉ ሲሆኑ ተያያዥነታውም የሚከተለውን ይመስላል።

.




ከላይ ለማየት እንደሚቻለው ተግባራቱ እርስ በርስ የሚገናኙ፣ የሚደጋገፉና ወደ አንድ አቅጣጫ ማለትም  መሻሻልን አልመው የሚንቀሳቀሱ ናቸው። የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት መሻሻል መገለጫው የተማሪዎች ውጤት መሻሻል ነው። ስለዚህ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት መሻሻል ጣቢያዎች መሠረታዊግብም እነኚህየአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት መሻሻል መርሃ-ግብር ጣቢያዎች አራቱን ቁልፍ መሠረታዊ የትምህርት ቤት ጉዳዮች በተጠናከረ መልኩ ማከናወንና የተማሪዎችን ውጤት ማሻሻል ነው፡፡

### 1.1.2 የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት መሻሻል መርሃ-ግብር አስፈላጊነት

በአገራችን ድህነትን ለመቀነስ ትምህርትን እንደ አንድ ዓብይ መሣሪያ በመጠቀም ጥረት እየተደረገባለበት በአሁኑ ወቅት በአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች ደረጃ ያለውን የመማር ማስተማር ሥራ ማሻሻል ከትምህርት የሚጠበቀውን ውጤት ለማሳደግ የሚኖረው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው።

የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት መሻሻል መርሃ-ግብርን በአገራችን እንዲተገበር በማድረግ፡-

- የአ.መ.ት ጣቢያዎችን አመቻቾችንና አመራር ኮሚቴ የሥራ ብቃት፣ ቅልጥፍናና ተነሳሽነት በተለያዩ ዘዴዎች በማሳደግ (ዕርስ በርስ በመማማር፣ በመገማገም ድክመትን በማስወገድና ጠንካራውን የበለጠ በማሳደግ፣ የልምድ ልውውጥ በማደረግ፣ ተጨባጭና ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ሥልጠና በመስጠት ወዘተ..) የትምህርት አሰጣጥን ለማሻሻል ያስችላል፤
- ለተማሪዎች ምቹ የትምህርት ሁኔታና አካባቢ እንዲኖር፣ የጐደሉትን ደረጃ በደረጃ በማሟላት ለትምህርት ያላቸውን ፍላጐት እንዲጨምር ማድረግና የትምህርት አቀባበላቸውንም እንዲሻሻል ማድረግ ያስችላል፤
- ወላጆችና ኅብረተሰቡ ለትምህርት ያላቸውን ግንዛቤ በተለያዩ ዘዴዎች በማሳደግ ተሳትፎአቸውን ማጐልበትና ለትምህርቱ ሥራ የባለቤትነት መንፈስ እንዲኖራቸው ማድረግ ያስችላል፤
- ለትምህርቱ ሥራ አስፈላጊ የሆኑትን ግብዓቶች ከመንግሥት ከሚደረገው ድጋፍ በተጨማሪ ኅብረተሰቡን በማስተባበር መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን፣ ግብረሰናይ ተቋሞችንና የሃይማኖት ድርጅቶችን በማስተባበር ደረጃ በደረጃ እንዲሟሉ በማድረግ ትምህርቱ በጥራት እንዲሰጥ ማድረግ ያስችላል።

በዚህም ተማሪዎች ለትምህርት ያላቸው ተነሳሽነትና ፍቅር እንዲጨምር በማድረግ የትምህርት ብክነት ለመቀነስ ማለትም፣ የደጋሚና የሚያቋርጡ ተማሪዎች ቁጥር በመቀነስ ጥቅም ይኖረዋል።

### 1.1.3 የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ መሻሻል መርሀ ግብር ዓላማ

- የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ጥራቱን እንዲጠብቅ በማድረግ የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል፣ ውጤትና ሥነ-ምግባር ማሻሻል፣
- የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መርሀ ግብር አተገባበር በሁሉም አካባቢዎች ወጥነት ያለው እንዲሆን ማድረግ፣

- በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መስጫ ጣቢያ ደረጃ ያልተማከለ ስትራቴጂክ እቅድ በማዘጋጀት  እድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ህፃናት በተለይም ሴት ህጻናት በሙሉ የትምህርት እድል እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፣

## 1.2 የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ መሻሻል መርሃ-ግብር የትኩረት አቅጣጫ

በአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች የሚሰጠው ትምህርት ከመጀመሪያ ደረጃ የመጀመርያ እርከን ከሚሰጠው የትምህርት መርሀ ግብር ጋር በአቻነት የሚሰጥ በመሆኑ ተመሳሳይ የትኩረት አቅጣጫ ይኖረዋል። በመሆኑም የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ማሻሻል መርሀ ግብር ዓላማዎችን ለማሳካት በጣቢያ ማሻሻል ማእቀፍ ውስጥ የተካተቱትን አበይት ርዕሰ ጉዳዮች  በመመርኮዝ ይሆናል።

እነሱም፦

- መማርና ማስተማር፣
- ምቹ የትምህርት ሁኔታና አካባቢ ፣
- የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት አመራርና አስተዳደር፣
- የህብረተሰብ ተሣትፎ ናቸው፡፡

እነዚህ አበይት ርዕሰ ጉዳዮችም የሚያተኩሩባቸው ዋና ዋና ነጥቦች የሚከተሉት ይሆናሉ።

### 1.2.1 መማርና ማስተማር

#### 1.2.1.1 የውጤታማ አመቻቾች ጥረትና ተነሳሽነት

ለአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት መሻሻልና የተማሪዎች ውጤት እድገት በትምህርት ሥራ ከተሠማሩት አካላት መካከል አመቻቾች ይበልጥ ቀዳሚውን ሥፍራ የሚይዙ ናቸው።ስለሆነም አመቻቾቹ በቂ እውቀት፣ ክህሎትና ሙያዊ ሥነ ምግባር (code of ethics) ኖሯቸው እሱንም አክብረው ኃላፊነታቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል። ከዚህም ባሻገር ለጣቢያው መሻሻል መርሃ-ግብር አመቻቾች ሊያከናውኗቸው የሚገቡ ውጤታማ ሥራዎችን በሚመለከት በተለያዩ ባህሪያት እንደሚከተለው ይሆናሉ።

## ሀ. አመቻቾች ስለሚያስተምሩት ትምህርት ይዘትና አቀራረብ ጠንቅቀው ማወቅ

ምንም እንኳን የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ አመቻቾች የትምህርት ዝግጁነታቸው አነስተኛ መሆኑ የሚታመን ቢሆንም በመጀመርያ ደረጃ አንደኛ ሳይክል የሚሰጡ ትምህርቶችን በብቃት ማስተማር የሚያስችል አካዳሚክ እውቀት ኖሯቸው የማስተማሩን ሥራ በማቀድ ይተገብራሉ። በመማር- ማስተማር ሂደቱም አሳታፊ የማስተማር ሥነ-ዘዴና የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ሥራ ላይ ማዋል ይጠበቅባቸዋል። የእድሜ ልዩነት ባለበት ክፍል ውስጥ ማሰተማር መቻልና በተማሪዎች መካከል ያለውን የትምህርት አቀባበልና የመማር ልዩነቶችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በተለያዩ አቀራረቦች ተማሪዎችን የማስተናገድ ብቃት ሊኖራቸው ይገባል።

## ለ.ተማሪዎች ስለሚማሩት ትምህርት በቂ ዕውቀት፣ ክሕሎትና አመለካከት ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ ወቅታዊና ተከታታይ ምዘናና ግምገማ ማድረግ

አመቻቾች ለተማሪዎቻቸው ከይዘቱ ጋር አግባብነት ያለው ሦስቱን የትምህርት ባህርያት (ዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት) ያካተቱ የክፍል መልመጃ፣ የቤት ሥራ፣ አጫጭር የግል ወይም የቡድን ሙከራዎች ወዘተ… በመስጠት ውጤታቸውን መዝግቦ መያዝና ግብረ መልስ መስጠት አለባቸው። በዚህም ደከም የሚሉ ተማሪዎችን በሚይዙት መረጃ በመለየት የተለየ ድጋፍ መስጠት፣ ከወላጆችም ጋር መወያየት የአንድ አመቻች ሙያዊ ግዴታ ነዉ።

## መ. ለውጤታማ የመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎችን የማነቃቃት ባህል መኖር

ተማሪዎች ከፍርሃት፣ ከጭንቀትና ከሥጋት ነፃ ሆነው ተዝናንተው ሲማሩ የበለጠ ሊተጉና ለተሻለ ውጤት ሊያመጡ እንደሚችሉ የተለያዩ የሥነልቦና ጥናቶች ያሰገነዝባሉ። በዚህ ረገድ ተማሪዎች በሚማሩት ትምህርት ያልገባቸውን እንዲጠይቁ ማበረታታት፣ ተማሪዎች ለሚጠየቁት ጥያቄ የሚሰጡት ምላሽ የተሳሳተ ቢሆንም አለማሸማቀቅ፣ በራስ የመተማመን ባህልን ማዳበር እና ስሜታቸውን መጠበቅ እንዲችሉ ሁሉም አመቻቾች ይህን አቀራረብ በተግባር ማዋል ይጠበቅባቸዋል።

በተጨማሪም በክፍል የተማሩትን ትምህርት እንዲያዳብሩ ትምህርታዊ ጉብኝት ማዘጋጀትና ማስጐብኘት፣ የተሻለ ውጤት የሚያስመዘግቡና በክፍል ውሰጥም የተሻለ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ ተማሪዎችን በመለየት አቅም በፈቀደ መጠን የማበረታቻ ሽልማት መሰጠት፣ በመማር ማሰተማር ሂደት ከተማሪዎች ለሚቀርቡ ሃሣብና አስተያየቶች አክብሮት በመስጠት በአዎንታዊ መልክ መቀበልና መወያየት፣ ለተማሪዎች በሚገባቸው ቋንቋ (friendly and simple language) በመጠቀም የትምህርቱን መልዕክት ማስተላለፍ የተማሪዎችን የመማር ስሜት የሚያነቃቃ ስለሆነ አመቻቹ እነዚህን መርሆዎች ዓፅንዖት ሰጥቶ በመጠቀም እንዲያስተምሩ ተገቢና ወቅታዊ ስልጠና በመስጠት አቅማቸውን የመገንባት ስራ ይሰራል።

### ሠ. አመቻች ለተማሪዎች አርአያ መሆን አለበት

አንድ አመቻች በአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች ግቢም ሆነ ውጪ በተማሪዎችና በአካባቢው ኅብረተሰብ እይታ ውስጥ የተመሰገነና ጥሩ ስነ-ምግባር ያለዉ መሆን አለበት። የዚህ ዓይነት ባህርይ ያላቸው አመቻቾች፡-

- የሚያስተምሩበትን ክፍል የዲሲፒሊን ሥርዓት በማስከበር ረገድ በአግባቡ የሚይዙና የሚመክሩ፣
- ንፅህናው የተጠበቀና በሕብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያለው የአለባበስ ሥርዓት ያላቸው፣
- ሰዓት በማክበርና ሳይቀሩ ዘወትር በሥራ ገበታቸው የሚገኙ፣
- በመማር-ማስተማር ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችን ለመፍታት ጥረት የሚያደርጉ፣
- በልዩ ልዩ ሱሶች ያልተጠመዱ፣
- የተማሪዎችን መብት የሚያከብሩና በፆታ፣ በዘር፣ በሃይማኖት፣ በአካል ጉዳት ምክንያት ልዩነት ሳያደርጉ ለተማሪዎች ተገቢውን ድጋፍ የሚሰጡ፣
- ከሥራ ባልደረቦቻቸው ጋር ተግባብተው በመቀናጀትና በመደጋገፍ የሚሰሩ፣
- የሕግ የበላይነትን የሚቀበሉና ተግባራዊ የሚያደርጉ፣
- የዲሞክራሲ አስተሳሰቦችን የሚያራምዱ፣

### ረ. የፆታ፣ የልዩ ፍላጐትና የችሎታ ልዩነትን መረዳት መቻል

አመቻቾች፡-

- በክፍል ውሰጥ ሲያስተምሩ ለሴትም ሆነ ለወንድ የሚሆን ተስማሚና ተገቢ ቋንቋ (friendly language) መጠቀም እና
- በትምህርት አቀባበል በተማሪዎች መካከል ያለውን ልዩነትና የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች መኖራቸውን በመረዳት ተገቢ ድጋፍ መስጠት ይጠበቅባቸዋል።

### 1.2.1.2 የተማሪዎች ጥረትና የሚጠበቅባቸው ባህሪያት

ውጤታማ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች መሻሻል ወይንም ለውጥ ሊመጣ ከሚችልባቸው ዋነኛ ጉዳዮች መካከል አንዱ የተማሪዎች የራሳቸው ብርቱ ጥረት ተጠቃሽ ነው። በዚህ ረገድ ተማሪዎች በጥሩ ዲሲፒሊን ታንፀው የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያውን ደንብና ሥነ-ሥርዓት በማክበር ትምህርታቸውን በንቃት መከታተልና ለጥሩ ውጤት በትጋት መሥራት ይኖርባቸዋል። በመሆኑም በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚከተሉት ባህሪያት እንዲኖራቸው ይጠበቅባቸዋል።

- በቡድን በመሥራት እርስ በርስ በመረዳዳትና በመማማር የሚሰሩ፣
- ለአመቻቾችና ለትምህርት መስጫ ጣቢያው አመራር አክብሮት ያላቸውና የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች የሚወዱ በዚህም የተነሳ ትርፍ ጊዜያቸውን የቱቶሪያል ፕሮግራሞች ላይ የሚያሳልፉ፣
- በትምህርት መስጫ ጣቢያው ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጪ በአመቻቾቹ የሚሰጠውን ትምህርት በጥሞና የሚከታተሉ፣ ከጣቢያው ያለበቂ ምክንያት የማይቀሩ፣ መልመጃዎችንና የቤት ሥራዎችን በጊዜ ሠርተው የሚያቀርቡ፣
- የትምህርት መስጫ ጣቢያው ኃላፊዎችና አመቻቾች የሚሰጡትን ምክር፣ ድጋፍና ደንብ በአግባቡ የሚፈጽሙ፤
- ለአመቻቾችና ለጣቢያው ጓደኞቻቸው ተገቢውን አክብሮት የሚሰጡ፣
- ለትምህርት መስጫ ጣቢያውም ሆነ ለህብረተሰቡ ታማኝነታቸውን በተግባር የሚያረጋግጡ፤
- ሥነ-ሥርዓትን የተከተሉ፣ አለባበስና አካላዊ ንፅህናቸውን የጠበቁ፣ በሌሎች ጓደኞቻቸው ዘንድም በመልካም አርአያነት የሚጠቀሱ ሆነው መገኘት አለባቸው።

#### 1.2.1.3 ሥርዓተ ትምህርት፡-

ሥርዓተ ትምህርቱ

- አፍ መፍቻ ቋንቋን
- እንግሊዝኛን
- ሒሳብን
- አካባቢ ሳይንስንና እስቴቲክስ ትምህርቶች በጣቢያ ማሻሻል መርሀ ግብር የሚተገበሩ ይሆናሉ።

በነዚህ የትምህርት አይነቶች ትኩረት በመስጠት አግባብነት ያለው ክፍለ ጊዜ እንዲመደብላቸውና በመፃህፍት አቅርቦትም ቅድሚያ እንዲሰጣቸው ይደረጋል።

የትምህርት አሰጣጡም በችግር ፈቺነት ላይ ያተኮረ ሆኖ ተማሪዎች ልዩ ልዩ መልመጃዎችን እየሰሩ፣ እየጠየቁ፣ ዕውቀትና ክህሎት የሚቀስሙበት ተማሪ ተኮር ዘዴንና የተከታታይ ምዘና ሥርዓትን በተገቢው መንገድ ሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል።

### 1.2.2 የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ አመራርና አስተዳደር

የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች ለተማሪዎች ውጤት መሻሻል ከፍተኛ ሚና መጫወት እንዲችሉ ተገቢውን የማስተባበርና የመምራትን ሥራ ማከናወን ይጠበቅባቸዋል።

የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ አመራርና አስተዳደር  የሚያካትታቸው፦

- የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ ሃላፊ አመቻች/ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያው ርዕሰ መምህር ሊሆን ይችላል፡፡
- በአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያው ያሉ የትምህርት ኮሚቴዎች (የቀበሌ ሊቀመንበር፣ የአካባቢው የሀገር ሽማግሌዎች፣ የጎሳ ባላባቶች፣ የሀይማኖት መሪዎች፣ የልማት ጣቢያ ባለሙያዎች)፣
- ከአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች ውጭ ያሉ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅት ተወካዮች ናቸው፡፡

እነዚህ አካላት  ቀጣይነት ያለውን የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች መሻሻል ለማምጣት ግንባር ቀደም ሚና መጫወት ይጠበቅባቸዋል። በዚህ ረገድ ለሚከሰቱ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች ችግሮችና ድክመቶች የመጀመሪያ ተጠያቂ የሚሆኑት እነዚህ አካላት ሲሆኑ በአንፃሩም ለችግሮች ቁልፍ መፍትሔ በማስገኘት ውጤታማ አሠራርና ተሞክሮ በማምጣት በኩልም ተገቢውን ሚና ይጫወታሉ። በአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት መስጫ ጣቢያ ከመደበኛው ትምህርት ቤቶች ጋር የሚስተካከል አደረጃጀቶች የማይኖሩ በመሆኑ ከላይ የአስተዳደር ሚና የሚጫወቱ አካላት በጣቢያ መሻሻል ኮሚቴነትም ያገለግላሉ።

ከዚህ አንፃርም ከጣቢያው መሻሻል ኮሚቴ ጋር በመሆን እድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ህጻናትን ወደ ጣቢያው ለማምጣት፣  ህጻናቱም እንዳያቋርጡና ለጣቢያውም መሻሻል የሚረዱ ግብአቶችን ለሚሟላት ህብረተሰቡን በማሳተፍ የህጻናትን ማንበብ፣ መፃፍ፣ ማስላት የሚያሻሽል እቅድ አዘጋጅተው መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል።

### 1.2.3 ምቹ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ ሁኔታና አካባቢ

የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ አካባቢ ለመማር ማስተማሩ እንቅስቃሴ ምቹና ጤናማ መሆን ለትምህርቱ በጥራት መሰጠት ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡

በዚህም መሠረት፡-

- ተማሪዎች ያለምንም ስጋት ተረጋግተው መማር የሚችሉበት፤ ደህንነቱ የተጠበቀና ሠላም የሰፈነበት፣ ትንኮሳ ጠለፋና አስገድዶ መድፈር የሌለበት፣ የተማሪዎች ዲሲፒሊን በአግባቡ የተያዘበት፣ በተማሪዎችና በአመቻቾች መካከል ጤናማ ግንኙነት ያለበት ይሆናል።
- አስፈላጊ የትምህርት ፋሲሊቲዎች ማለትም በቂ የመማሪያ ክፍሎች/ሥፍራዎች፣ የመማሪያ ማስተማሪያ መፃሕፍት፣ ማጣቀሻ መፃሕፍትና የመጫወቻ ሥፍራዎች እና የመሳሰሉት እንዲገኙ ይደረጋል።
- ተማሪዎች የመማር ችግሮቻቸው ላይ ተወያይተው መፍትሄ ለማግኘት የሚችሉበት ሥርዓት ይዘረጋል።

- አካዳሚያዊ በሆነ ጉዳይ የመወሰን ሁኔታ በአመዛኙ የአመቻቾቹ ድርሻ ይሆናል።
- የክላስተር ትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከላት ለአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች ተገቢነታቸውን የጠበቁ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ደረጃ በደረጃ እንዲሟሉላቸው ያደርጋሉ።
- አቅም በፈቀደው መጠን የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች ንፁህ የመጠጥ ውሃ አገልግሎት፣ ለአመቻቾች፣ ለወንድና ለሴት ተማሪዎች የተለያየ የመፀዳጃ ቤት፣ አጥርና የራሳቸው ግቢ እንዲኖራቸው ይደረጋል።

### 1.2.4 የወላጅ፣ የህብረተሰብ፣ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ ግንኙነት እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አጋርነት

ለአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ መሻሻል የወላጅ፣ የኅብረተሰብና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ድርሻ ከፍተኛ ነው።

**ሀ. የወላጆችን ክትትል/ትኩረት በተመለከተ፤**

የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ የተማሪ ወላጆች ስለልጆቻቸው የመማር ሁኔታ ለመከታተል የሚከተሉት ነጥቦች መፈፀም ይጠበቅባቸዋል።

- የተማሪዎችን የትምህርት መሣሪያዎችን ማሟላት'
- የልጆቻቸውን ንፅህና መጠበቅ'
- የልጆቻቸውን የጣቢያ ውሎ ክትትል ማድረግ እንዲሁም
- ወላጆች ሥለልጆቻቸው ዲሲፒሊን ችግሮች፣ ስለሴቶች የትምህርት ተሳትፎ፣ ስለሚያቋርጡና በትምህርታቸው ደከም ስለሚሉ ተማሪዎች… ዙሪያ ከአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ ሀላፊዎችና አመቻቾች ጋር በመወያየት ችግሮቹን በጋራ እንዲፈቱ ይጠበቃል።

**ለ. የወላጆች፣ የህብረተሰብና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የፋይናንስና የማቴሪያል ድጋፍ**

ትምህርትን በስፋት ለማዳረስ፣ ጥራቱን ለማሻሻል፣ ተገቢነቱንም ለማረጋገጥ እና ችግሮችን ለመፍታት ስለሚደረገው ጥረት መንግሥት ብቻውን ሊወጣው እንደማይችል

የታወቀ ነው። ስለሆነም የኅብረተሰቡና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አጋርነት ታክሎበት ኅብረተሰቡ ለትምህርት ሥራ ያለውን ባለቤትነት የበለጠ በማጠናከር የፋይናንስና የማቴሪያል ድጋፍ በማድረግ  በማቋቋም፣ ለአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች ተጨማሪ ክፍሎችን በመገንባት፣ ነባሮችንም በማደስ፣ የትምህርት ግብአቶችን በማሟላት ረገድ ተገቢውን ተሳትፎ በማድረግ አጋርነቱንና ባለቤትነቱን እንዲያረጋግጥ ሥርዐት ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

## 1.3 የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ መሻሻል የአተገባበር ስልት

### 1.3.1 ዋና ዋና ስልቶች

የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ መሻሻል መርሃ-ግብር አተገባበርን በተሳካ ሁኔታ ለመፈፀም ቀጥሎ የተዘረዘሩት የአፈጻጸም ሥልቶች ሁሉም የትምህርት ዘርፍ አካላትና ጣቢያዎች በዋነኛነትን ሊጠቀሙባቸው ይገባል።

- ከሁሉ አስቀድሞ በአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ መሻሻል ኮሚቴ  ደረጃ ለአመቻቾች ፣ ለተማሪዎች፣ ለወላጆችና ለህብረተሰቡ ስለፕሮግራሙ ምንነት፣ ዓላማና ጠቀሜታ አስቀድሞ ሥልጠና በመስጠት የሁሉንም የጋራ ተሳትፎ በማስተባበር በጋራ መንቀሳቀስ፣
- የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎችንጥንካሬዎንና ድክመቶችን ለይቶ በማወቅ የጋራ ዕቅድ መንደፍ፣
- ችግሮችን ለይቶ በማውጣት ቅደም ተከተል ማስያዝና የድርጊት መርሀ-ግብር አዘጋጅቶ መንቀሳቀስ፣
- ለአተገባበሩ ተጨማሪ የበጀት ምንጭ (ከህብረተሰቡና ከአጋር አካላት)  በማፈላለግ ተግባራዊ ማድረግ፣
- ፕሮግራሙን እውን ለማድረግ የክትትልና የግምገማ የጊዜ ሠሌዳ አዘጋጅቶ መንቀሳቀስ፣
- በወረዳና በክላስተር ደረጃ ከአቻ አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች እንዲሁም ከመደበኛ ትምህርት ቤቶች ጋር የልምድ ልውውጥ በማድረግ መልካም ተሞክሮዎችን በጣቢያው ተግባራዊ ማድረግ፣

- በአርብቶ አደር አካባቢዎች ህብረተሰቡ ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላ አካባቢ በሚንቀሳቀሱበት ወቅት ወይም በሌሎች ምክንያቶች ተማሪዎች እንዳያቋርጡ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ያቋረጡትን የማስመለስ ስራዎችን መስራት
- በየዓመቱ ቢያንስ ሁለት ጊዜ የየሴሚስተር ውጤቶች ከታዩ በኋላ የምክክር ስብሰባዎችን በአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች ደረጃ ማካሔድና በየጊዜው ለሚነሱ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ተገቢውን ምላሽ በመስጠት የማስተካከያ ርምጃ መውሰድ፣

## 1.4 የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ መሻሻል መርሃ-ግብርን የሚመራ ኮሚቴ ማቋቋም

- ለአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች ባለድርሻዎች፡- አመቻቾችን፣ ተማሪዎችን፣ ወላጆችንና ህብረተሰቡን እንዲሁም ለጣቢያው ድጋፍና እገዛ የሚያደረጉ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካሎችን፣ የሃይማኖት ድርጅቶች በመለየት በጣቢያ መሻሻል አስፈላጊነት ላይ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች ሀላፊ አመቻች ወይም የክላስተር ሱፐርቫይዘር ወይም የአጎራባች መደበኛ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር ለተለዩት ባለድርሻ አካላት ግንዛቤው የመፍጠር ኃላፊነት አለባቸው።
- የሚቋቋመው የጣቢያ መሻሻል ኮሚቴ አባላት ከአመቻቾች፣ ከወላጆች፣ ከሀይማኖት መሪዎችና የጎሳ ባላባቶች የተውጣጡ ሆነው ከአምስት እስከ ሰባት አባላት ያሉት ሆኖ የጣቢያው አመቻች ሀላፊ/ርዕሰ መምህር የኮሚቴው ሰብሳቢ ይሆናል።
- የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች መሻሻል ኮሚቴ እንደ ተቋቋሞ በቅድሚያ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ በማውጣት እና ሥራውን ለማስጀመርና ለማካሄድ የሚያስችለው ዝርዝር የሥራ ፕሮግራም መንደፍ አለበት።

## 1.5 የአማራጭ መሠረታዊ ጣቢያ ግለ ግምገማ ማካሄድ

የአማራጭ መሠረታዊ ጣቢያ ግምገማ የራስ ቅጽ ያለው ሲሆን በየደረጃው ያሉ- የጣቢያው ማህበረሰብ አባለት በግለ ግምገማው መሳተፍ ይጠበቅባቸዋል። የጣበያ ግምገማ ማተኮር ያለበቸው ጉዳዬች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

- የጣቢያውን አመቻች ያሳተፉ የክትትልና ግምገማ ስልጠና እንዲሰጥና እንዲተገበር ማድረግ
- የመማር ማስተማሩን ሂደት ሊያሻሽልና የትኩረት አቅጣጫና ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዬችን ሊያሳይ በሚችል የጣቢያ ግለግምገማ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ
- ጣቢያዎቹ በሚያደርጓቸው ግለ- ግምገማና ከለሳዎች ሁሉ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ የመማር ማስተማሩ ጥራት እና የተማሪዎች ውጤት መሻሻል ላይ መሆኑን ማረጋገጥ፣
- ሁሉም አመቻቾችና ወላጆች በግለ ግምገማው በመሳተፍ ከሚገኘው የልምድ፣የጋራ ግንዛቤና ለቀጣይ ስራ የመነሳሳት ጥቅም መጋራታቸውን ማረጋገጥ፣
- ለቀጣዩ እንቅስቃሴያቸው እንዲያመቻቸው ከግለ ግምገማው የተገኘውን ውጤት በተደራጀና ሁሉም ሊረዳው በሚችል መልክ ለትም/ቤቱ እና ለየአካባቢው ህ/ሰብ ማሳወቅ፣
- በግለ ግምገማ ውጤት መሰረት መሻሻል በሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ላይ በቂ እርምጃ መውሰድ፣በተጨማሪም የጣቢያው ዕቅድ እነዚህን ጉዳዮች በቀዳሚነት ያካተተ መሆኑን ማረጋገጥ፣
- ወቅታዊ የሆነ የክፍል ምልከታ በማድረግ የትምህርት አሰጣጡን ጥራትና የአፈጻጸም ችግሮችን መከታተል፣መገምገምና ጉድለት በሚታይበት አካባቢ ስልጠና ጨምሮ መሰል ድጋፍ በወቅቱና በአግባቡ መስጠት።

## 1.6 ምዘና የአፈጻጸም ትንተና ግብ ማስቀመጥ

- የአማራጭ መሠረታዊ የትምህርት ጣቢያ ምዘና፣የአፈፃፀም ትንተና ግብ በሚያስቀምጡበት ወቅት በሚከተሉት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ትኩረት በመሰጠት መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል።
- የጣቢያውን አመቻችቶ ለምዘና፣ በመረጃ ትንተና ማህደር ተግባር /Portfolio/ በማዘጋጀትና ግብ በማስቀመጥ ረገድ በቂ ክህሎት ማዳበራቸውን ማረጋገጥ፣
- የሚከናወኑ ምዘናዎችንና ግምገማዎችን ውጤት በመተንተን ለዕቅድ ዝግጅት እንደግብዓት መጠቀም፣

- በተማሪ በሴክሽን በክፍልና በትምህርት አይነት ደረጃ የሚታዩ ዝቅተኛ ዉጤትን ለይቶ ማወቅ፣
- ተለይተው በታወቁና ውጤትን ለማሻሻል በተማሪ፣በሴክሽን፤ በክፍልና በትምህርት አይነቶች በታዩ ዝቅተኛ ውጤቶች ላይ የተመሰረቱ የማሻሻል ተግባራትን በጣቢያ መሻሻል ዕቅድ ውስጥ ማካተት ፣
- የተማሪዎችን በየዕለቱና በሰዓቱ ስለመገኘታቸው የመከታተያ ስልት ቀይሶ በመተግበር የቀሪ ተማሪዎችን መጠን በከፍተኛ ደረጃ ለመቀነስ አልሞ መንቀሳቀስ፣
- ጣቢያው በተለያዩ የጣቢያ መሻሻል ርዕሰ ጉዳዬች የሚያስቀምጠውን ግብ ለጣቢያው ማህበረሰብና ለአካባቢው ህብረተሰብ ማሳወቅ፣
- ወላጆች የተማሪዎችን ውጤት ለማሻሻል በሚታቀዱ ግቦችና ፕሮግራሞች ላይ በሚዘጋጁ ውይይቶች እንዲሳተፉ ማድረግ፣
- ተማሪዎች ከተቀመጡት ግቦች አንጻር የሚያሳዩትን መሻሻል ለውጥ መከታታል፣መገምገምና ጉድለት በሚታይበት አካባቢ ሰልጠናን ጨምሮ መስል ድጋፍ በወቅቱና በአግባቡ መሰጠት፡፡

## 1.7 የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ መሻሻል ዕቅድ ማዘጋጀት

### የዕቅድ ዝግጅት ሂደት

- በቅድሚያ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች ለሚሰጧቸው ጉዳዮች ዓላማዎችን፣ ስልቶችን፣ ግብዓቶችን፣ የጊዜ ገደብን፣ ፈፃሚዎችን እና የመገምገሚያ ስልቶችን ያካተተ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ መሻሻል መርሃ-ግብር ዕቅድ መንደፍ፣
- የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ መሻሻል መርሃ-ግብር ዕቅድ ቀጣይነት ያለውና የጣቢያውን መሻሻል ሊያመጣ የሚችል መሆኑን ማረጋገጥ፣
- የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ መሻሻል መርሃ-ግብር ዕቅድ በአተገባበሩ ፍፃሜ ሊደረስባቸው የተቀመጡትን ግቦች ሊያመጣ የሚችልና

በውይይት ወቅት የለያቸውን መሻሻል የሚገባቸው ጉዳዮችን መሠረት ያደረገ መሆኑን ማረጋገጥ፣

- ለአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ መሻሻል የሚሰጠውን ድጋፍ ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግ እንዲረዳ ከትምህርት ጽ/ቤቶችና ከክላስተር ማእከላት የሚቀርቡ መጠይቆችን በወቅቱና ባግባቡ ሞልቶ መመለስ፣

**በዕቅዱ ውስጥ ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ ጉዳዮች**

- እድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ህጻናት በሙሉ ወደ ጣቢያው መምጣታቸውን ማረጋገጥ
- ተማሪ-ተኮር የትምህርት አሰጣጥ ሥርዓት በሥራ ላይ መዋሉን የሚያመላክት ዕቅድ መኖሩን ማረጋገጥ፣
- የተከታታይ ምዘናና የትምህርት አቀባበል ክትትል ሥርዓት መዘርጋቱን የሚያመላክት መሆኑን፣
- በአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ የሚያስተምሩ አመቻቾች እርሰ በርስ እንዲደጋገፉና የክፍል ውስጥ ምልከታ የሚያካሂዱ መሆኑን፣
- የሴት ተማሪዎችን ተሳትፎና ብቃት ሊያሳድግ የሚችል ዕቅድ መነደፉን፣
- ልዩ የትምህርት ፍላጐት ያላቸውን ሕፃናት የመለየትና ፍላጐታቸውን የማሟላት ተግባር ለማከናወን የሚያስችል ዕቅድ መነደፉን፣
- የተማሪዎች ማቋረጥን ለመቀነስ የሚደረጉ ድጋፎችና ክትትሎችን ያካተተ መሆኑን፣
- የተማሪዎችን የማንበብ፣ የመፃፍ፣ የማስላት እና አካባቢያቸውን የመግለጽ ችሎታቸውን ለማሳደግ የሚያስችሉ ተግባራትን ያካተተ መሆኑን፣
- የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ መሻሻል ዕቅድ ውስጥ የጣቢያ አመራር ኮሚቴ አካላት ወሳኝ ሚና መጫወታቸውን ማረጋገጥ፣

## 1.8 ሥርዓተ ትምህርቱን በውጤታማነት መተግበር

ተማሪዎች ተገቢ የሆነና ደረጃውን የጠበቀ ትምህርት እንዲያገኙ ለማስቻል ትምህርት ቤቶች ለትምህርቱ አሰጣጥና ውጤታቸውንም ለማሻሻል የሚረዱ ወሳኝ የሆኑ ግብአቶችን ደረጃ በደረጃ እንዲሟሉ ማድረግና የመማር ማስተማር ሂደቱንም በየጊዜው እየተፈሹ ማሻሻል ይጠበቅባቸዋል። በዚህም መሠረት ሥርዓተ ትምህርቱን በተመለከተ ጣቢያዎች የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ይኖርባቸዋል።

- አመቻቾች የመማርያ ማስተማርያ መፃህፍት ከአካባቢያቸው ጋር የተገናዘበ መሆኑን በመገምገም ግብረ-መልስ እንዲሰጡ አስፈላጊውን ሁሉ እገዛ ማድረግ፣
- ተማሪዎች በተጓዳኝ ትምህርት እንደ ሙዚቃ ክበብ፣ ድራማ፣ ስፖርት፣ ጤና፣ የአካባቢ እንክብካቤ ክበብ እና በመሳሰሉት እንዲሳተፉ ማድረግ፣
- አመቻቾች በአግባቡ መሰልጠናቸውንና ሥርዓተ ትምህርቱን በሥራ ለመተርጐም መሰማራታቸውን ማረጋገጥ፣ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣
- ወላጆች የልጆቻቸውን የመማር ሁኔታ (ትምህርት) መደገፍ (ማገዝ) እንዲችሉ ማበረታታት፣


# ክፍል ሁለት፡- የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ መሻሻል መርሀ-ግብር ማእቀፍ

የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት መሻሻል መርሃ ግብር ማዕቀፍ ጣቢያ በወጡት ስታንዳርዶች መሰረት፤ ምን ያህል ውጤታማ መሆናቸውን ለመከታተል የሚያስችሉ መሣሪያዎችንና ሂደቶችን የያዘ ሥርዓት ነው። ማዕቀፉ ጣቢያዎች ያሉበትን ደረጃ ምን እንደሚመስል በተለያዩ ተጨባጭ መረጃዎች የሚያውቁበት፣ ወደፊት ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ለይተው ማወቅ የሚችሉበት እና ምን ዓይነት ተጨባጭ የሆነ ውጤት ለማምጣት እንደሚፈልጉ አቅደው የሚንቀሳቀሱበት የትግበራ መመሪያ ከመሆኑም በላይ በዋናነት የሚከተሉት መሣሪያዎች ይገኙበታል።

- የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች ራሳቸውን ገምግመው ያሉበትን ደረጃ ለማወቅ የሚያስችሏቸው የግምገማ መሣሪያዎች፣
- የዳሰሳ ጥናት ለማካሄድ ከአመቻቾች፣ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ አመራር ኮሚቴ እና ከወላጆች መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችሉ መሣሪያዎች፣
- መረጃ ለመሰብሰብ፣/ ለማጠናቀርና ሪፖርት ለማድረግ የሚያስችሉ ቅጾች ናቸው።

የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎቹ ከላይ የተጠቀሱትን መሣሪያዎች በመጠቀም በአጠቃላይ ማቀድ፣ መተግበር፣ መከታተልና መቆጣጠር፣ መመርመርና መከለስ እንዲሁም ለባለድርሻዎች ሪፖርት ማድረግ ያስችላቸዋል። ይህ ሂደት የማያቋርጥ፣ ዑደታዊና በየሦስት ዓመቱ ጉዳዩ በሚመለከተው ከጣቢያ ውጭ ባለ አካል ግምገማ ተካሂዶበት በሚሰጠው አስተያየት መሠረት ማስተካከያ እየተደረገበት የሚከናወን ነው። ይህን ዑደታዊ ክንውን በሚከተለው አኳኋን መግለጽ ይቻላል።

**የጣቢያ መሻሻል ዑደት**




## 2.1 የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች ማሻሻል ስታንዳርድ

በአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች እንዲሁም በሌሎችም አካባቢዎች በተለያዩ ምክንያቶች በመደበኛው የትምህርት አቅርቦት ስልት የመጀመርያ ደረጃ ትምህርት እድል ያላገኙ ህጻናትና ወጣቶች የትምህርት እድል ለመስጠት እንዲቻል የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት መርሀ ግብር ተቀርጾ ወደ ትግበራ ተገብቷል። ይህ

መርሀ ግብር የሚካሄድባቸው ጣቢያዎች ሊያሟሏቸው የሚገቡ ስታንዳርዶች ከነትግበራ ጠቋሚዎቻቸው በአራት ዐቢይ ርዕሰ ጉዳዮች ተከፍለው ከዚህ በታች በዝርዝር ቀርበዋል።

## ዐብይ ርዕሰ ጉዳይ 1፦መማርና ማስተማር

ጥራት ያለው መማርና ማስተማር በተጨባጭ መረጃ ላይ ተመስርቶ የወደፊቱን ያገናዘበና ችሎታው የዳበረ የተማረ ማህበረሰብ የሚፈጥር ከመሆኑም በላይ አመቻቾችና ተማሪዎች የላቀ ብቃት ለመሻትና ዕምቅ ችሎታቸውን ለመጠቀም ከፍተኛ ጥረት የሚያደርጉበት ክንውን ነው፡፡

### ንኡስ ጉዳይ 1.1፡-የማስተማር ተግባር

**ስታንዳርድ 1 ፦ የአመቻቾች እውቀት፣ ክህሎትና እሴቶች በተለያዩ ስልጠናዎች አድገው በማስተማር ተግባር ጥቅም ላይ ውለዋል።**

**የትግበራ ጠቋሚዎች**

1.1 አመቻቾች ተማሪዎቻቸውየተለያየ የመማር ፍጥነት እንዳላቸው በመቀበል የማስተማር ዘዴዎቻቸውን በዚሁ መሠረት አስተካክለው በመጠቀም የተማሪዎቹን ውጤት አሻሽለዋል።

1.2 አመቻቾች ለተማሪዎቻቸው ጥሩ ተምሳሌት ናቸው።

1.3 አመቻቾች ልዩ የመማር ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች የተለያዩ ዘዴዎች ተጠቅመው ቀደም ብለው ለይተው ድጋፍ በመስጠታቸው የትምህርት አቀባበላቸው ተሻሽሏል።

1.4 አመቻቾች በየእለቱ በጣቢያው በመገኘት የመማር ማስተማሩን ተግባር እንዲከናወኑ ድጋፍ ተደርጓል።

1.5 አመቻቾች በሚያስተምሩበት የትምህርት ዓይነቶች የትምህርት እቅድ (ሳምንታዊና ዓመታዊ) አዘጋጅተው እንዲያስተምሩ ድጋፍ ተደርጓል።

1.6 አመቻቾች ከትምህርቱ ይዘት ጋር የሚዛመድ አካባቢዊ የሆነ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን አዘጋጅተው እንዲጠቀሙ ተደርጓል።

**ስታንዳርድ 2፦ አመቻቾች ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የተማሩትን ትምህርት ከአካባቢያቸው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር እንዲያገናዝቡ በማድረግ እውቀታቸውና ክህሎታቸው አድጓል።**

**የትግበራ ጠቋሚዎች**

2.1 አመቻቾች የክፍል ትምህርቱን ተማሪዎቻቸው ከተጨባጭ የህይወት ተሞክሮቻቸው ጋር እንዲያገናዝቡ አድርገዋል፣

## ንኡስ ጉዳይ 1.2፡-መማርና ግምገማ

**ስታንዳርድ 3 ፦የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያው ለተማሪዎች የላቀ ውጤት መምጣት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠቱ ለውጤት መሻሻል መሠረት ሆኗል።**

**የትግበራ ጠቋሚዎች**

1.1 የተማሪዎቻቸውን እውቀትና ክህሎት ለማሳደግ የተከታታይ ምዘና አካሂደዋል።

1.2 የተማሪዎቻቸውን የተከታታይ ምዘና ውጤት በሮስተር ተደራጅቷል። ውጤታቸውም በተማሪ ሪፖርት ካርድ ተዘጋጅቶ ወላጆች እንዲያውቁት ተደርጓል።

1.3 የተማሪዎችን የተከታታይ ምዘና ውጤት መሰረት በማድረግ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ተማሪዎች ለይቶ እገዛ በመደረጉ ውጤታቸው እንዲሻሻል ተደርጓል።

## ንኡስ ጉዳይ 1.3 ሥርዓተ ትምህርት

**ስታንዳርድ 4፦ሥርዓተ ትምህርቱ ትርጉም ያለው፣ አሳታፊ እና የተማሪዎቹን የእድገት ደረጃና ፍላጎቶች ያገናዘበ ለመሆኑ የመመርመርና የማሻሻል ሂደቶች አሉ።**

**የትግበራ ጠቋሚዎች**

4.1 ለሁሉም ተማሪዎች በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች የመማርያና ማስተማርያ መፅሐፍት 1ለ1 ደርሷል።

4.2 አመቻቾች የመማርያ ማስተማርያ መፃህፍት ከአካባቢያቸው ጋር የተገናዘበ መሆኑን በመገምገም ግብረ-መልስ እንዲሰጡ እገዛ ተደርጓል።

## ዐብይ ርዕሰ ጉዳይ 2፦ምቹ የትምህርት ሁኔታና አካባቢ

የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት መስጫ ጣቢያዎች ከመደበኛው ጋር የሚመጣጠን መሰረተ ልማት ባይኖራቸውም ለእያንዳንዱ ተማሪ ፍላጐት ተስማሚ የሆነና ምቹ የሆነ አካባቢ ሊፈጠር ይገባል።

### ንኡስ ጉዳይ 2.1፦- የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ ፋሲሊቲ

**ስታንዳርድ** 5፦የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያውለደረጃው የተቀመጠውን ስታንዳርድ የጠበቁ ፋሲሊቲዎችን በማሟላቱ የጣቢያው አመቻቾች ሥራቸውን በአግባቡ ለማከናወን፣ ተማሪዎችም ለመማር አስችሏቸዋል።

**የትግበራ ጠቋሚዎች**

5.1 መማሪያ ክፍሎች/ማስተማርያ ስፍራዎች ተማሪዎችን ለመማር የሚያነቃቁና ምቹ በመሆናቸው የተማሪዎቹን የመማር ፍላጐት አነሳስተዋል።

5.2 የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች (መማሪያ ክፍሎች ፣የአመቻቾች ቢሮ፣ የእቃ ግምጃ ቤት፣ መፀዳጃ ቤት- የሴትና የወንድ የተለየ) ተሟልተዋል።

5.3 ንጹህ የመጠጥ ውሃ እንዲኖር ተደርጓል።

5.4 መጫወቻ ሜዳ እንዲኖር ተደርጓል።

5.5 የትምህርት መስጫ ጣቢያውን ማስከበር የሚችል አጥር (በአካባቢው በቀላሉ ከሚገኝ ቁሳቁስ የሚሠራ) በህብረተሰብ ተሳትፎ ተዘጋጅቷል።

5.6 የሰንደቅ ዓላማ መስቀያ ቦታና የሰልፍ ሥነ-ሥርዓት ማስከበሪያ ሥፍራ ተዘጋጅቷል።

## ንኡስ ጉዳይ 2.2 ተማሪን ማብቃት

**ስታደንርድ** 7 አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ የተለያዩ የአደራጃጃቶች የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋቱ በተማሪዎች ዘንድ ኃላፊነትን የመውስድና ራስን በዲሰፕሊን የመምራት ልምድ ዳብሯል፡፡

**የትግበራ ጠቋሚዎች**

7.1 አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ጣቢያ በውሳኔዎች አሳጣጥ ላይ የተማሪዎችን ተሳትፎ በማሳደጉ የተማሪዎች ኃላፊነትን የመውሰድና በዲስፕሊን የመመራት ባህል ደብሯል፡፡

7.2 በመማሩ ሂደት ተማሪው ኃላፊነት የሚሰማው፣በራሱ የሚተማመን ነፃነት የሚሰማወና ተቀበይነት እንደለው የደሳስ ጥናቶች አመልክተዋል፡፡

7.3 አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ ተማሪዎችን በአመራረ ላይ እንዲሳተፉ ለሁሉም ፆታዎች እኩል ዕድል ሰጥቷል፡፡

## ንዑስ ጉዳይ 2.3 ለተማሪ የሚደረግ ድጋፍ

**ስታንደርድ** 8 አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ጣቢያ አካባቢያቸው ለሁሉም ተማሪዎች ምቹ ፣ የማያሰጉ፣ ደገፊ እና የተማሪዎችን ፊላጎት የሚያሟሉ በመሆናቸው ተማሪዎች በትምህርታቸው ስኬታማ ሆነዋል፤፤

**ትግበራ ጠቋሚዎች**

8.1 በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ጣቢያ የሚከናወኑ ማናቸውም የትምህርት ሥራዎች ከሁሉም በላይ ቀደሚ አድርገው የተንቀሳቀሱት የተማረውን የመማር ፍላጎት ማሟላትና ውጤት ማሻሻል ላይ መሆኑ ተረጋገጧል፤፤

8.2 አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ጣቢያ ለተማሪዎች የሚያደርገው ሁለንተናዊ ድጋፍ የትምህርት ብክነትን እንዲቀንስ አድርጓል፡፡

8. 3 አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ጣቢያ ምቹና የማያሰጋ መሆኑን ከትም/ ቤቱ ማህበረሰብና ከወላጆች የተሰበሰቡ መረጃዎች ያመለከታሉ፡፡

## ዓቢይ ርዕሰ ጉዳይ 3 ፦የጣቢያ አመራር

አመራር የጋራ ኃላፊነትን የሚጠይቅ ተግባር ነው። የጣቢያ አመራር እቅድ በማዘጋጀትና ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር በመተባበር ደንቦችን በማውጣት እድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ህጻናትን ወደ ትምህርት ቤት ለማምጣትና የተማሪዎችን መጠነ ማቋረጥ ማሻሻል ይኖርበታል። ራዕዩ ተማሪን ማዕከል ያደረገ እና ለአመቻቾች ትኩረት በመስጠት ተከታታይ መሻሻልን ማስገኘት ነው።

### ንኡስ ጉዳይ 3.1፡- ስትራተጂካዊ ራዕይ

**ስታንዳርድ 6፦** በጣቢያው የነበሩ ጥንካሬዎችና ድክመቶችን ለይቶ በማወቅ የጋራ ዕቅድ ተነድፏል።

**የትግበራ ጠቋሚዎች**

6.1 የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያው የነበሩ ጥንካሬዎችና ድክመቶችን በመለየት ስትራተጂካዊና ዓመታዊ እቅዶች በአሳታፊነት አዘጋጅቷል።

6.2 የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያው ችግሮችን ለይቶ በማውጣት ቅደም ተከተል በማስያዝ የድርጊት መርሀ-ግብር አዘጋጅቷል።

### ንኡስ ጉዳይ 3.2፡-የመሪነት ባህሪይ

**ስታንዳርድ 7፦**የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያውየእርስ በርስ ሙያዊ መማማሪያ የሚካሄድበት ተቋም በመሆኑ የአመቻቾችና የአመራር ሙያዊ ብቃት ተሻሽሏል ።

**የትግበራ ጠቋሚዎች**

7.1 ክትትልና ድጋፍ የሚደረግበት ሥርዓት በመዘርጋቱ የአመቻቾች ሙያዊ ብቃት ተሻሽላል ።

7.2 የትምህርት ቤቱ አመራር የሥልጠና ፍላጐቶች ተለይተዋል፣ እንዲሁም የአመራር አባላቱ በሥልጠና ፕሮግራሞች ለመሳተፍ ችለዋል።

7.3 ትምህርት ቤቱ የአሠራርና የግጭት አፈታት ሂደቶችን የሚገልጽ ሙያዊ ደንብ/ህግ አለው።

## ዓቢይ ርዕሰ ጉዳይ 4፡-የህብረተሰብ ተሳትፎ

ጥራት ያለው አጋርነትንና የግንኙነት መረብን ከወላጆችና ከህብረተሰቡ ጋር መፍጠር ትምህርት ቤቶች ተማሪዎቻቸውን ከህብረተሰቡ ጋር ለማቀራረብ (ለማገናኘት) ያስችላቸዋል። እውነተኛና ቀጣይነት ያለው አጋርነት ትምህርት ቤቶች ለህብረተሰቡ መረጃዎች ለመስጠትና ህብረተሰቡ ለሚጠብቃቸው ትልሞች ምላሽ ለመስጠት ይረዳቸዋል።

## ንኡስጉዳይ 4.1፡- ከወላጆችና ከአሳዳጊዎች ጋር አብሮ መስራት

**ስታንዳርድ 8፡- ወላጆችና አሳዳጊዎች በልጆቻቸው ትምህርት ጉዳዮች በንቃት መሳተፋቸው የተማሪዎችን መማር አጐልብቷል።**

**የትግበራ ጠቋሚዎች**

8.1 ሁሉም ወላጆች ልጆቻቸው ወደ ጣቢያው እንዲልኩና እንዳያቋርጡ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ተዘርግቷል።

8.2 የወላጆች ተሳትፎን ለመደገፍ ወቅታዊ መድረኮችን ጣቢያው አዘጋጅቷል። ጣቢያው በሚጠራው ስብሰባዎች ላይ እንዲሳተፉም ተበረታተዋል ።

8.3 ወላጆች የልጆቻቸውን የቤት ሥራ በመመልከት አስተያየት ሰጥተዋል።

## ንኡስ ጉዳይ 4.2፡-ኅብረተሰብን ማሳተፍ፡-

**ስታንዳርድ 9፡-ትምህርት ቤቱ ከኅብረተሰቡ እና ከውጭ ድርጅቶች ጋር ተባብሮ የመስራት ልምድ በመጠናከሩ ውጤታማ አጋርነት ተፈጥሯል።**

**የትግበራ ጠቋሚዎች**

9.1 ጣቢያው በሚያስፈልገው ሀብቶች ላይ በቂ ተሳትፎ ማድረግ እንዲችል ወርሃዊ /እንደ አስፈላጊነቱ/ መድረክ ተዘርግቷል።

9.2 ለወላጆችና ለህብረተሰቡ ትምህርት ለመስጠትና ሌሎች ድጋፎች/ማንበብና መፃፍን ማስተማር፣ ጐጂ ልምዶችን ማስወገድ፣ ልማት ነክ ተግባራትን ማከናወን ወዘተ/ ለማድረግ ጣቢያው ፕሮግራም በማውጣት ተግባራዊ በማድረጉ ውጤታማ አጋርነት ተፈጥሯል።

9.3 ከጣቢያው ውጭ ያሉ ተቋሞችና ድርጅቶች (የመደበኛ ትምህርት ቤቶች፣ የልማት ጣቢያ ሰራተኞች፣ የልማት አጋሮች) ለመማር-ማስተማሩ ሥራ ልምዶቻቸውን በማካፈል ድጋፍ ሰጥተዋል።

## ንኡስጉዳይ 4.3፡- የትምህርቱን ስራ ማስተዋወቅ

**ስታንዳርድ 10፦** የጣቢያውን እንቅስቃሴዎች በመልካምነታቸውና በጠቃሚነታቸው ለውጭው ኅብረተሰብ የማስተዋወቅ ሥራ በመሠራቱ በትምህርት ቤቱ ሥራ ላይ የማህበረሰቡ ግንዛቤ ዳብሯል፤ ድጋፍም ጨምሯል።

**ትግበራ ጠቋሚዎች**

10.1 የትምህርት ቤቱ ስኬታማ ክንውኖች አከባበር ተደርጎላቸዋል።

10.2 በትምህርት ዓመቱ መጀመርያ የትምህርት ሳምንትና በትምህርት ዓመቱ

10.3 በሴሚስተሩ ማጠናቀቂያ የወላጆች በዓል አከባበር

# ተቀጽላዎች

## 1.1፡- የጣቢያ መገምገሚያ ናሙና ቅጽ

| የትግበራ ጠቋሚ | የአፈፃፀም ደረጃ | | |
|---|---|---|---|
| | ከፍተኛ | መካከለኛ | ዝቅተኛ |
| አመቻቾች ተማሪዎቻቸው የተለያየ የመማር ፍጥነት እንዳላቸው በመቀበል የማስተማር ዘዴዎቻቸውን በዚሁ መሠረት አስተካክለው በመጠቀም የተማሪዎቹን ውጤት አሻሽለዋል። | | | |
| አመቻቾች ለተማሪዎቻቸው ጥሩ ተምሳሌት ናቸው። | | | |
| አመቻቾች ልዩ የመማር ፍላጐት ያላቸውን ተማሪዎች የተለያዩ ዘዴዎች ተጠቅመው ቀደም ብለው ለይተው ድጋፍ በመስጠታቸው የትምህርት አቀባበላቸው ተሻሽሏል። አመቻቾች በየእለቱ በጣቢያው በመገኘት የመማር ማስተማሩን ተግባር እንዲከናወኑ ድጋፍ ተደርጓል። | | | |

| የትግበራ ጠቋሚ | የአፈፃፀም ደረጃ | | |
|---|---|---|---|
| | ከፍተኛ | መካከለኛ | ዝቅተኛ |
| አመቻቾች በሚያስተምሩበት የትምህርት ዓይነቶች የትምህርት እቅድ (ሳምንታዊና ዓመታዊ) አዘጋጅተው እንዲያስተምሩ ድጋፍ ተደርጓል። | | | |
| አመቻቾች ከትምህርቱ ይዘት ጋር የሚዛመድ አካባቢዊ የሆነ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን አዘጋጅተው እንዲጠቀሙ ተደርጓል። | | | |
| አመቻቾች የክፍል ትምህርቱን ተማሪዎቻቸው ከተጨባጭ የህይወት ተሞክሮቻቸው ጋር እንዲያገናዝቡ አድርገዋል፣ | | | |
| ጣቢያዎች የተማሪዎቻቸውን እውቀትና ክህሎት ለማሳደግ የተከታታይ ምዘና አካሂደዋል። | | | |
| የተማሪዎቻቸውን የተከታታይ ምዘና ውጤት በሮስተር ተደራጅቷል። ውጤታቸውም በተማሪ ሪፖርት ካርድ ተዘጋጅቶ ወላጆች እንዲያውቁት ተደርጓል።<br>የተማሪዎችን የተከታታይ ምዘና ውጤት መሰረት በማድረግ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ተማሪዎች ለይቶ እገዛ በመደረጉ ውጤታቸው እንዲሻሻል ተደርጓል። | | | |
| ለሁሉም ተማሪዎች በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች የመማርያና ማስተማርያ መፅሐፍት 1ለ1 ደርሷል። | | | |
| አመቻቾች የመማርያ ማስተማርያ መፃህፍት ከአካባቢያቸው ጋር የተገናዘበ መሆኑን በመገምገም ግብረ-መልስ እንዲሰጡ እገዛ ተደርጓል። | | | |
| መማሪያ ክፍሎች/ማስተማርያ ስፍራዎች ተማሪዎችን ለመማር የሚያነቃቁና ምቹ በመሆናቸው የተማሪዎቹን የመማር ፍላጎት አነሳስተዋል። | | | |
| የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች (መማሪያ ክፍሎች ፣የአመቻቾች | | | |

| የትግበራ ጠቋሚ | የአፈፃፀም ደረጃ | | |
|---|---|---|---|
| | ከፍተኛ | መካከለኛ | ዝቅተኛ |
| ቢሮ፣ የእቃ ግምጃ ቤት፣ መፀዳጃ ቤት- የሴትና የወንድ የተለየ) ተሟልተዋል። | | | |
| ንጹህ የመጠጥ ውሃ አገልግሎት፣የሕፃናት መጫወቻ ሜዳ እንዲኖር ተደርጓል። | | | |
| የትምህርት መስጫ ጣቢያውን ማስከበር የሚችል አጥር (በአካባቢው በቀላሉ ከሚገኝ ቁሳቁስ የሚሠራ) በህብረተሰብ ተሳትፎ ተዘጋጅቷል። | | | |
| የሰንደቅ ዓላማ መስቀያ ቦታና የሰልፍ ሥነ-ሥርዓት ማስከበሪያ ሥፍራ ተዘጋጅቷል። | | | |
| ጣቢያው የነበሩ ጥንካሬዎችና ድክመቶችን በመለየት ስትራተጂካዊና ዓመታዊ እቅዶች በአሳታፊነት ተዘግጅቷል። | | | |
| ችግሮችን ለይቶ በማውጣት ቅደም ተከተል በማስያዝ የድርጊት መርሀ-ግብር አዘጋጅቷል። | | | |
| ለጣቢያውአመቻቾች የተሻለ ልምድ ባላቸው አመቻቾች ሥልጠና/እገዛ (coaching and mentoring) የሚደረግላቸው ሥርዓት በመዘርጋቱ የአመቻቾች ሙያዊ ብቃት ተሻሽላል። | | | |
| የትምህርት ቤቱ አመራር የሥልጠና ፍላጐቶች ተለይተዋል፤ እንዲሁም የአመራር አባላቱ በሥልጠና ፕሮግራሞች ለመሳተፍ ችለዋል። | | | |
| ትምህርት ቤቱ የአሠራርና የግጭት አፈታት ሂደቶችን የሚገልጽ ሙያዊ ደንብ/ህግ አለው። | | | |
| ጣቢያው ከክላስተር ማዕከል እና ከሌሎች የአካባቢው ተቋሞች ሪሶርሶችንና የሠለጠኑ ባለሙያዎችን በመጠቀሙ የመማር ማስተማሩ ሂደት ተሻሽሏል ። | | | |
| ሁሉም ወላጆች ልጆቻቸው ወደ ጣቢያው እንዲልኩና | | | |

| የትግበራ ጠቋሚ | የአፈፃፀም ደረጃ | | |
|---|---|---|---|
| | ከፍተኛ | መካከለኛ | ዝቅተኛ |
| እንዳያቋርጡ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ተዘርግቷል። | | | |
| የወላጆች ተሳትፎን ለመደገፍ ወቅታዊ መድረኮችን ጣቢያው አዘጋጅቷል። ጣቢያው በሚጠራው ስብሰባዎች ላይ እንዲሳተፉም ተበረታተዋል ። | | | |
| ወላጆች የልጆቻቸውን የቤት ሥራ በመመልከት አስተያየት ሰጥተዋል። | | | |
| ጣቢያው በሚያስፈልገው ሀብቶች ላይ በቂ ተሳትፎ ማድረግ እንዲችል ወርሃዊ /እንደ አስፈላጊነቱ/ መድረክ ተዘርግቷል። | | | |
| ለወላጆችና ለህብረተሰቡ ትምህርት ለመስጠትና ሌሎች ድጋፎች/ማንበብና መፃፍን ማስተማር፣ ጐጂ ልምዶችን ማስወገድ፣ ልማት ነክ ተግባራትን ማከናወን ወዘተ/ ለማድረግ ጣቢያው ፕሮግራም በማውጣት ተግባራዊ በማድረጉ ውጤታማ አጋርነት ተፈጥሯል። | | | |
| ከጣቢያው ውጭ ያሉ ተቋሞችና ድርጅቶች (የመደበኛ ትምህርት ቤቶች፣ የልማት ጣቢያ ሰራተኞች፣የልማት አጋሮች) ለመማር-ማስተማሩ ሥራ ልምዶቻቸውን በማካፈል ድጋፍ ሰጥተዋል። | | | |
| የትምህርት ቤቱ ስኬታማ ክንውኖች አከባበር ተደርጎላቸዋል። | | | |
| በትምህርት ዓመቱ መጀመርያ የትምህርት ሳምንትና በትምህርት ዓመቱ ማጠናቀቂያ የወላጆች በዓል አከባበር ተከናውኗል። | | | |

## 1.2፡- የሦስት ዓመት ስትራቴጅ ክዕቅድ ማቅረቢያ ናሙና ቅጽ

የጣቢያው ስም፡-

የሦስት ዓመት ዕቅድ 2008-2010

ዐብይ ርዕሰ -ጉዳይ፡- መማር ማስተማር

ንዑስ ርዕሰ -ጉዳይ፡-

ግብ፡-

ዓላማዎች፡-

| የሚከናወኑ ተግባራት | በኃላፊነት የሚያከናውነው አካል | ተግባሩን ለማከናወን የሚያስፈልገው ገንዘብ | የክንውን ጊዜ | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | 2008 ዓ.ም | 2009 ዓ.ም | 2010 ዓ.ም |
| ሁሉም ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያው እንዲልኩና እንዳያቋርጡ ተከታተይ የዉይይት መድርኮች ማዘጋጀትና አስመላሽ ኮሚቴ ማቋቋም። | የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ | -- | X | X | X |
| ንጹህ የመጠጥ ውሃ አገልግሎት፣ የሕፃናት መጫወቻ ሜዳ እንዲኖር ማድረግ። | የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ እና አመራር ኮሚቴ | -- | X | X | X |
| አመቻቾች ከትምህርቱ ይዘት | አመቻቾች | -- | X | X | X |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ጋር የሚዛመድ አካባቢዊ የሆነ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ማዘጋጀት። | | | | | |

ዐብይ ርዕሰ -ጉዳይ፡- ምቹ የትምህርት ሁኔታ
ንዑስ ርዕሰ -ጉዳይ ______
ግብ፡- ______
ዓላማዎች፡- ______

| የሚከናወኑ ተግባራት | በኃላፊነት የሚያከ ናውነው አካል | ተግባሩን ለማከናወን የሚያስፈልገው ገንዘብ | የክንውን ጊዜ | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | 2008 ዓ.ም | 2009 ዓ.ም | 2010 ዓ.ም |
| 5.7 የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች (መማሪያ ክፍሎች፣ የአመቻቾች ቢሮ፣ የእቃ ግምጃ ቤት፣ መፀዳጃ ቤት- የሴትና የወንድ የተለየ) ማሟላት። | የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ እና አመራር ኮሚቴ | -- | x | x | x |
| | | | | | |
| | | | | | |

ዐብይ ርዕሰ -ጉዳይ፡- የህብረተሰብ ተሳትፎ
ንዑስ ርዕሰ -ጉዳይ______
ግብ፡-______
ዓላማዎች፡-______

| የሚከናወኑ ተግባራት | በኃላፊነት የሚያከ | ተግባሩን ለማከናወን | የክንውንጊዜ |
|---|---|---|---|

| | ኃላፊነት የሚያከ ናውነው አካል | የሚያስፈልገው ገንዘብ | 2008 ዓ.ም | 2009 ዓ.ም | 2010 ዓ.ም |
|---|---|---|---|---|---|
| የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያው ከህብረተሰቡና ከውጫዊ ድርጅቶች ጋር ተባብሮ መስራት | የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ እና አመራር ኮሚቴ | | | | |
| | | | | | |

ዐብይ ርዕሰ -ጉዳይ የጣቢያ አመራር
ንዑስ ርዕሰ -ጉዳይ____________________
ግብ፦_________________________
ዓላማዎች፦__________________________

| የሚከናወኑ ተግባራት | በኃላፊነት የሚያከ ናውነው አካል | ተግባሩን ለማከናወን የሚያስፈልገው ገንዘብ | የክንውንጊዜ | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | 2008 ዓ.ም | 2009 ዓ.ም | 2010 ዓ.ም |
| የትምህርት ቤቱን ውስጠ ደንብ፣ መመሪያዎችንና የአሰራር ስርዓቶችን አደራጅቶ ስራ ላይ ማዋል፡፡ | የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ እና አመራር ኮሚቴ | - | x | x | x |
| | | | | | |
| | | | | | |

## 1.3፡-የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጣቢያ መሻሻል ዓመታዊ የድርጊት መርሃ-ግብር ናሙና ቅጽ

ዐብይ ርዕሰ -ጉዳይ መማርማስተማር
ንዑስ ርዕሰ -ጉዳይ____________________

ግብ፦ ___________________________
ዓላማዎች፦ ______________________

| የሚከናወኑ ተግባራት | በኃላፊነት የሚያከ ናውነው አካል | ተግባሩን ለማከናወን የሚያስፈልገው ገንዘብ | የክንውንጊዜ | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | 2008 ዓ.ም | 2009 ዓ.ም | 2010 ዓ.ም |
| | | | | | |
| | | | | | |

ከተግባሩ የሚጠበቅ ውጤት ___________________________________________

___________________________________________

ውጤታማ ክንውኖች እንዴት ይገመገማሉ? ___________________________
___________________________________________

የቡድኑ አባላት አስተያየት ___________________________________________
___________________________________________
___________________________________________
___________________________________________

## 1.4፡- የተለያዩ የመማር ፍጥነት ያላቸው ተማሪዎች መከታተያ ቅጽ

| ተ.ቁ | የአመቻቹ/ቿ ሥም | የምታስተምረው /የሚያስተምረው/ ትምህርት ዓይነት | የምታስተምረው /የሚያስተምረው/ ክፍልና ደረጃ | የትምህርት አቀባበልና ፍጥነት | | | | | | | | | ተማሪዎችን ለመለየት /የተቀመጠበት/ የተጠቀመችበት ዘዴ | ደረጃውን ለማሻሻል የተደረጉ ጥረቶች | የተገኙ ውጤቶች | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዝቅተኛ | | | መካከለኛ | | | ፈጣን | | | | | | |
| | | | | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | |

የመምህሩ/ሯ ተጨማሪ አስተያየት________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

የትምህርትዘርፍ/ ዲፓርትመንት ተጠሪ አስተያየትና ማረጋገጫ____________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

## 1.5፡- ተከታታይ የመምህራን ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ስልጠናን / CPD / መከታተያ ቅጽ

| ተ.ቁ | በት/ቤት ያሉመምህራን ብዛት | | | አዲስ የተቀጠሩ መምህራን ብዛት | | | በት/ቤትያሉ Mentors ብዛት | ለCPD የተሰጠ የሥልጠና ዓይነት | ዓላማው | የተሳፊዎችብዛት | | | | | | ስልጠናው የወሰደውጊዜ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | ነባር | | | አዲስ | | | | |
| | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | | | | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | |

ሥልጠናው በትክክል ለመካሄድ የተሰጠ ማረጋገጫ____________________________________________________________

_________________________________________________________________________________

## 1.6፡- የክበባትና የልዩልዩ ፕሮግራሞች እንቅስቃሴ መከታተየያ ቅጽ

**የክበቡ/ የፕሮግራሙ ዓይነት** -------------------------------------------------------------------

**የክበቡ ተጠሪ /የፕሮግራሙ አስተባባሪ ስም** ---------------------------------------------------- **ፊርማ** -----------------------------------

| ተ.ቁ | ቀን | የክንውኑ ዓይነት | በክንውኑ የተሳተፉ አባላት ብዛት | | | | | | ለት/ቤቱ/ለህብረተሰብ ያስገኘው ፋይዳ | እንቅስቃሴው የወሰደው ጊዜ | ሪፖርቱ የቀረበበ ትጊዜ | ሪፖርቱን ያረጋገጠው ክፍል | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ተማሪዎች | | | መምህራን | | | | | | ስም | ፊርማ | |
| | | | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | |

ሀ/ በእንቅስቃሴ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች——————————————————————————————————————————————————————

ለ/ ችግሮችን ለመፍታት የተወሰዱ እርምጃዎች——————————————————————————————————————————

ሐ/ የተጓዳኝ ትምህርት ኮሚቴ አስተያየትና ፊርማ——————————————————————————————————————

## 1.7፡- የተማሪዎች ውጤት መከታተያ ቅጽ

**የት/ቤት ስም ----------------------------------------------------------------- ውጤቱ የተመዘገበበት ዘመን ---------------------------------------------**

**ሰሚስተር ---------------------------------------------------------- የክፍል ደረጃው -----------------------------------------------------------**

| ተ.ቁ | የት/ዓይነት | ከ0-49 | | | ከ50-74 | | | ከ75-100 | | | ጠቅላላ የተማሪዎችብዛት | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | |
| | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | |

ሀ. በዲፓርትመንት ተጠሪው የተማሪዎችን ውጤት ካለፈው የት/ዘመን ጋር በማነጻጸር የተሰጠ አስተያየት——————————————

ለ. ያጋጠሙ ችግሮች————————————————————————————————————————————————————

ሐ. የተሰጡ መፍትሄዎች——————————————————————————————————————————————————

መ. ተጨማሪ አስተያየቶች ካሉ____________________________________________________________________________________________________________________________________________________

ሪፖርቱን ያረጋገጠው ኃላፊ ስምና ፊርማ ------------------------

## 1.8 የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት መስጫ ጣቢያዎች የማጠናከሪያ ትምህርት መቆጣጠሪያ ቅጽ

1/ የመምህሩ/ሯስም______________የት/ዓይነት__________________________

በማጠናከሪያ የተሳተፉ ተማሪዎች ክፍልና ደረጃ________ብዛት _______ወንድ______ሴት_______

2/ የማጠናከሪያው ትምህርት ዓላማ፡- ___________________________________________________________________________________

3/ የማጠናከሪያው ትምህርትይዘት________________________________________________________________________________________

4/ የማጠናከሪያው ትምህርት የፈጀው ጊዜ__________________________________________________________________________________________

5/ ለማጠናከሪያው ትምህርት መምህሩ የተጠቀመበት ስልት

________________________________________________________________________________

6/ በትምህርቱ አሰጣጥ ወቅት ያጋጠመ ችግር

________________________________________________________________________________

7/ የተሰጠ መፍትሔ

______________________________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________

8/ በማጠናከሪያ ትምህርት የተገኘ ውጤት

_________________________________________________________________

ያረጋገጠው ክፍል አስተያየትና ፊርማ _______________________________________

## 1.9፡- የሥርዓተ ትምህርት መሣሪያዎች ስለመገምገማቸው መከታተያ ቅጽ

**የትምህርት ቤቱ ስም -----------------------------------------------------------**

**የትም/ክፍል/ ዲፖርትመንቱ ስም -------------------------**

| ተ.ቁ | የተገመገመው የት/መሣሪያ ዓይነት | የገምጋሚው መምህር/ርት ወይም መምህራን ስም | የግምገማው ውጠት | የቀረበበት ጊዜ | ስለ ግምገማው ውጤት የተሰጠው አስተያየት | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |

## 1.10፡- ቅጽ ትምህርት ቤቱን የሚረዱ ወላጆች /አሳዳጊዎች/ ብዛት መመዝገቢያ ቅጽ

| ተ.ቁ | ትምህርት ቤቱ ከማህበረሰቡ ጋር ለመገናኘት የፈጠራቸው መደረኮች | የወላጅ ተሳትፎ ብዛት በፐርሰንት | የተደረጉ ድጋፎች | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በዓይነት | በገንዘብ | በጉልበት | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |